# ሞትም በጥላሁን አማረበት

ሞት! ታላቁ ሞት ለረዥም ጊዜ ተነፍጎት የነበረውን ክብር በጥላሁን አገኘው። ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሳር ሲያጭደው እንደ ቅጠል ሲያረግፈው ማንም ከቁም ነገር አልቆጠረውም ነበር። ይኸው በጥላሁን ማሸለብ ምክንያት በባንዲራ ተሸሞንሙኖ፣ በአበባ አጊጦ ሰማንያ ሚሊዮን ሕዝብን ሞትን አከበረው። የአበሻ ልጅ በሰፈረበት በመላው ዓለም ሀዘን የሁሉን ቤት ጎበኘው። ሞት በጥላሁን አማረበት። እንዲያውም ከልዕልት ዳያና ሞት የበለጠ ተከበርኩ ያለ እስኪመስል ድረስ ሆነ። በጥላሁን እረፍት የኢትዮጵያ ሕዝብ በድጋሚ አንድነቱን አስመሰከረ።

ከፉዎች፣ ጨቋኞች፣ አምባገነኖች፣ ሌቦች፣ ሸፍጠኞችና ገዳዮች የሕዝብ ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቁማቸው እንዲመሰክሩ ተፈረደባቸው። ለጥላሁን እየተለቀሰ ተዘፈነ እየተዘፈነም ተለቀሰለት። ጥላሁን ድምጹን አጥፍቶ ደህና ሁኑ አላለም። ሽኝቱን በራሱ ዜማ እያደማመቀው በአካል እንጂ በመንፈስ ከናንተው ጋር ነኝ እያለን ሄደ። ሄደ እንባ እያራጨን!! እንደምንወደው እየነገርነው እንደሚወደን እያዜመልን ቢቀድመንም እንደምንከተለው እያረጋገጥንለት ተመመ። ሞትና መለያየት አንድ አይደለም ብንለውም ሊሰማን አልፈቀደም በሌላው ዓለም ዳግመኛ መገናኘት ሊኖር እንደሚችል ሊያስተምረን በዕለተ ትንሣዔ ተለየን። የግማሽ ምዕተ አመት ጉዞው ተቋጨ።

ጥላሁን አገሩን ሕዝቡን ይወዳልና ልጅነቱንና ጉልምስናውን ሁሉ ለርሷ ቸረ። ስጋውንም ወደ አፈርዋ ለመመለስ ተጣደፈ። እናም አሜሪካንን ጥሎ ከነፈላት በእቅፍዋ ውስጥም ሆኖ አረፈ ወደ ማጎጸንዋም በአጀብ ተመለሰ።

“............. እንኳንስ ደስታዬን የሰውነቴን ሰው፣
እንኳን ነጻነቴን ጺጋ ክብሬን ትቼው፤
በእናት ሀገር ምድር በሚያውቀኝ በማውቀው፣
ስቃይ መከራዬን አንቺ ዘንድ ያድርገው።
እናት አለም ጡትሽ ታሪክ ምድርሽ ይጥራኝ፣
አደራሽን ይገዬ ለዐይነ ስጋሽ ያብቃኝ። .........” አላት እንባው መንትዮሽ በጉንጮቹ እየወረደላት። ጥላሁን

የተለየ ምንም አልጠየቀም ነበር የእናቱን ትንፋሽ ብቻ! የጠየቀው ኦክሲጅን ግን ተነፍጎት ማለፍ ተገደደ። ጥልዬ ኦክሲጅኑን ሳብ ሳብ አድርጎ በካርቦን ዳይ ኦክሳይዱ ነበር ድምጹን እያስረቀረቀ ያስጨፈረን ያስተማረንና ያዋደደን። ይህ ጀግና ግን ስስትና ክፋት በነገሰበት አገሩ ውስጥ ትንፋሽ አጥሮት ሞተብን። እናም ስቃይ መከራውን ከእርስዋ ጋር አድርጎ ተከተተ።

የኔ ልብ ደግሞ የዞረበት ሆነና ከጥላሁን ይልቅ ለቀብር ለወጣው ሰው ማልቀሱን መረጠ። የመጀመርያ እርዳታ እንኳ ማግኘት የማይችሉ፣ ቢታመሙ ስለመድህኒት ሳይሆን ስለ ሬሳ ሳጥን ማሰብ የሚገባቸውን ዘመዶቼን አስቤ አለቀስኩኝ። ለጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ አለቀስኩኝ ያውም ስቅስቅ ብዬ። አይን አውጣነታቸው እየገረመኝ ‘ለዶቼ ቤሌ’ የሚሉትን ሰማሁ። ጥላሁን የመጀመርያ እርዳታ አጥቶ በአረፈበት ሀገር ውስጥ ያሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ሀኪም ቤቶቹን ወና አድርገው ስለ ዘፈኑ ያላቸውን አስተያየት ሊነግሩን መስቀል አደባባይ መውጣታቸው አስለቀሰኝ።

በሞታቸው ዳንኪራ ለሚመታ ቀባሪ ለሌላቸው በህይወት እያሉም እንኳ ተደብቀውና ተሹለክልከው ለሚኖሩ የወያኔ መሪዎች አለቀስኩኝ። በስማቸው እንኳ ሳይጠሩ በ’ፌክ’ ስም ተጠርተው የ ‘ፌክ’ ሕይወት ኖረው ለሚያልፉት አዘንኩ። የገንዘብ ብዛት የጦር ብዛት አልቅሶ እንደማይሸኝ ያላወቁ ከፉዎችን ምህረት ማን ይለምንላቸው ይሆን? መጠላት ሁለት ሞት መሆኑን የሚያዩ እነርሱ ናቸውና ለቤተሰቦቻቸውና ለልጆቻቸውም ክፉኛ አዘንኩ። አገር አፍራሽ አገር ሻጭ እየተባሉ ስም የሌለው መቃብር አፉን ከፍቶ ለሚውጣቸው ክፉ የወያኔ መሪዎች አለቀስኩ።

ምንም እንኳ የፖለቲካ ትርፍ ከጅለው ያደረጉት መሆኑን ሆዳችን ቢያውቀውም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን፣ ያከበረውን እንደሚያከብር፣ የወደደውን እንደሚወድ አስተማራቸው። በጥላሁን ሞት እንደሚጠይቃቸውም ልብ አላሉት ይሆናል እንጂ ሀኪሙን ወደ ስደት ልኮ፣ ሆስፒታሎችን አዳክሞ አገር አፍርሶ ይህን ታላቅ ሰው በሀገሪቱ መዲና የመጀመርያ እርዳታ የሚሰጠው ሰው በማጣቱ ገደሉብን እንደሚል ማን በነገራቸው። ጥላሁን ሕክምና ካጣ ማን ነው ታክሞ የሚድን?

በጥላሁን እረፍት ቀን የሁዋልዮሽ ሄጄ አደገኛ ቦዘኔ ተብለው በአግአዚ የተጨፈጨፉትን ወገኖቼን ሁሉ አሰብኩ። ከትናንት ወዲያ በባድሜ በአገር ድንበር ማስከበር ስም መሰሪዎቹ ያስጨፈጨፉትን ወገኖች አሰብኩ። የመከላከያ ሰራዊት በሚል የወያኔ ጀሌ መሆን ተገድደው በወራሪነት ተፈርጀው በሶማሌ ምድር ደማቸው ደመ ከልብ የሆኑ ወገኖቼን አስቤ አለቀስኩኝ። ወላጅ መርዶውን ሳይሰማ የአውሬ መጫወቻ የሆኑትን ሁሉ አሰብኩ። ሬሳቸው እየተጎተተ መሳለቂያ የሆኑትን ወንድሞቼን እያሰብኩ አለቀስኩኝ። ያንን ነዋ ጥላሁን ያዜመልኝ። ለዚያም ነበራ በጉንጩቹ ሙሉ እንባው ሲወርድ

የነበረው። ጥላሁን ስሙ ሲነሳ ፍቅር፣ አገር፣ ሰላም፣ አንድነት፣ መተሳሰብ ነዋ የሚታወሰኝ። ለጥላሁን ባዜም እንጂ ባለቅስ ሀዘኔ እንዴት ይወጣልኛል? ማዜም ስል ደግሞ ለዚያ ወጣት ሀዘን የኔም ልብ ተሰበረ። ጥልዬ እንኮኮ ብሎ ያሳደገው ፋንታ ሚሪንዳ የገዛለት ጉብሉ በቅርብ ርቀት ቃሊቲ ሆኖ አባቱን፣ መምህሩን ሊሰናበተው ያልቻለውን ቴዲ አፍሮን አሰብ አደረግሁ። የቴዲ የልቡ ውስጥ እሳት እንዴት ሊጠፋለት ይችላል? እጥፍ ሀዘን ሲያሸክሙት እንባውስ እንዴት ይሆናል ትላላችሁ? ጥላሁንስ እንዴት ተተኪ ሊኖረው ይችላል? አይኔን በአይኔ አየሁ ያለውን እያሰበ ለግብአተ መሬቱ ሊገኝ ባለመቻሉ የሚሰማውን ሳስብ አዘንኩኝ። ሁሉም ባገር ነው ብሎ ዘፍኖ በሀገሩ ተቀበረባት በአጽሙ አጥር ሊሆናት ተቀላቀላት። ሀገር ለምናጣው ለኛ ግን ማን ያልቅስ? ሀገር ከዳር ከመሀል እያፈረሱ መኖርያ ሳይሆን መቀበሪያ እንኳ የሚያሳጡንን አሁንም ምርጫችንን አጥብበው ወይ ወደ ሞት ወይ ወደ ሰደትና እስር ቤት የሚነዱንን የወያኔ ገዥዎች ተሸክመን ከተጓዝን መጨረሻችን ምን ሊሆን እንደሚችል ሳስብ ለራሴም አለቀስኩኝ።

በሀዘን ወቅት መልካም ነገር መመኘት ደግ ነውና እኒህ ለክፋት የሚተጉ፣ ለሀገር ጥፋት የማይታክቱ፣ በትናንቱ ውስጥ እየኖሩ ነገን ማየት ለተሳናቸውና ከኢትዮጵያ ጠላቶች በላይ ለኢትዮጵያ ጥፋት የሚተጉ ሁሉ የንስሀ ጊዜና የጥላሁን አይነት ሽኝት ብመኝላቸው እናንተስ ነብስ ይማር አትሏቸው ይሆን? ሰርጉ፣ ድግሱ፣ ግብዣው በጠቅላላው ሕይወት በጥላሁን እንዳማረበት ሁሉ ሞትም በጥላሁን ከበረ። መኖርና መሞት የማይቀር ከሆነ ተወድዶና ተፈቅሮ በክብር ማለፍ ምንኛ ደስ ያሰኛል።

ጥላችን ከኛው ጋር አብሮን ይኖራል!! ነብሱን እግዚአብሄር በገነት ታኑርልን።


ዳኛቸው

biyadegelgne@hotmail.com